ይቤ ሥነ ጽሑፍ ዘካርያስ ፡
ይትባረክ እግዚአብሔር ዘአንሥአ ለነ ቀርነ መድኃኒትነ
ኃይለ ሥላሴ እምቤተ ዳዊት ገብሩ ።
ደዌ ተፈጠመ ወጥቶ አደባባይ
በኃይለ ሥላሴ በልዕልት ፀሐይ ።

ስንፍና ብልግና የሴቶች ጋኔን
መጽሐፍ ብታሳየው እቴጌ መነን ፡
ጥሏቸው በረረ በጥቂት ዘመን ።



አናቃፊውን ሁል እሾኽ ጉልጥምቱን
ጠቅል ጠርነልሃል አንት አስፋ ወሰን ።

ደ ራ ሲ ፡

እግዚአብሔር አደለን በታላቅ ምሕረት ፡
ጽሑፍ ለደራሲ ለንጉሥ መንግሥት ፡
በመንግሥቱ ሥራ ብዘባርቅ እኔ ፡
ውርደትን ለራሴ ነው እፍረት ለወገኔ ፡
ቋንቋውን ነው እንጂ አስተዳደርስ ፡
ልጁ የልጅ ልጁ የንጉሥ ይውረስ ።

ከዘር የመጣ ነው የንጉሡ ዘውድ ፡
የኔም ያባቴ ነው የቅኔ መንገድ ፡
ዓለም ሁል ይወርሳል ያባቱን ንብረት ፡
ይዘ ያቄየውን ርስትና ጉልት ፡
ሊቅ ሞገስ ደረሰ የሠራልኝ ቤት ፡
ቅኔ ነው ልውረሰው በታላቅ ትጋት ።

ቅ ኔ ፡

የጎብር አገር ጐጆ መግቢያና መውጫው ፡
ሊቃውንት የሠሩት ሁለት በር አለው ፡
ምንም ሁለት ቢሆን ሦስት አራትም ፡
ጠባብ ስለሆነ ደንቄር አይገባም ።
ተራ ግጥም ጻፊ መጥፎ ቀላዋጭ ፡
ገብቶም አይረዳ ይቄማል ከውጭ ፡
ለብሶ ቢጐማለል ጋቢን ድንቅርና ፡
ዝቅ ብሎ ካልገባ ታጥቆ በትሕትና ፡

በሀብቱ በልብሱ በዕድሜው ሽምግልና ፡
ቢነዛ ቢያወራ የትዕቢቱን ዝና ፡
አገፋሪው ዕውቀት ከበር ቁሚልና ፡
ለመግባት አይችልም የኩራት ጋዜና ፡
ስለዚህ ወንድሜ ስማኝ ልንገርህ ፡
ቅኔን ለመረዳት ከቤቱ ገብተህ ፡
ትሕትና ጥበብህን ባጭሩ ታጥቀህ ፡
ግባ ተከተለኝ እኔ ስመራህ ።

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

መ ቅ ድ ም ።

ለትምህርት በውጭ ሀገር በነበርንበት ጊዜ ማንኛቸውንም የተፈጥሮ ውበትን የሚገልጥ የግጥም መጽሐፍ ስናነብ በሰው ሠራሽ ዘይት ተወልውላ የምታብለጨልጭ ከንክ ሀገራቸውን ተወዳዳሪ የሌላት አስመስለው በመጻፋቸው ፤ እንደዚህ ሁኖ የተሞገሰው እንዴት ያለ ቦታ ይሆን ? በማለት ፡ የአንከሮ ማዕበል እያማታን ስንደርስ ጆሮ ትልቅ ወይን ትንሽ ይሆንብንና እንዲህ ያለው ገጣሚ ልምላሜ ቢያገኝ ኑሮ ምን ብሎ ይጽፍ ነበር ይሆን ? እያልን በማሰላሰል ወደ ተግባራችን ስንመለስ ፤ የሀገራችን ውበትና ቀጎጅና ትዝ ባለን ቀጥር ፤ የክረምቱ ዝናብ ሳያነግለው የበጋው ፀሐይ ሳያጠወልገው ዘመን ሳይለይ ዓመቱን ሙሉ ፡ የሚያብበው ዕፀብ ድንቅ አበባዋ ፤ ዘለዓለም ባረንጓዴ ቀለም የተነከረው ልምላሜዋ ፤ ጀንዲና ወላንሳ መሳዩ የብዙ ዕፀዋት ቅጠልዋ ፤ እንደ ስጋጃና ፍራሽ ተነጥፎ የተጐዘጐዘው ሣርዋ ፤ ሲረግጡት ተንበክ ተንበክ የሚለው አፈርዋ ፤ አልፎ ሃጁን ሁሉ ተንከባለሉብኝ ፤ ያላንዳች ምንጣፍ ተኙብኝ እያለ የሚጋብዘው ጨፈዋ ፤ በደንበኛ ግጥም ቢገለጥ እንዴት ይሆን ? የሚል ሐሳብ ስላደረብን ፤ ልማድ አድርገነው አናደንቀውም እንጂ ፤ ኢትዮጵያን በልምላሜ በኩል የሚወዳደራት ስለሌለ ፤ ውበቱ የኛ ሲሆን ግጥምና ቅኔማ ኢትዮጵያውያን የተረፋቸውን ይናኛሉ ብለን ፤ ወደ ውድ ሀገራችን እንደተመለስን ቀጎጅናዋን በቅኔ ጽፈን ለወገናችን እናበረክታለን ብለን ፤ ሐሳባችንን ቄርጠን ቃል ኪዳን ገባን ። ከዚህ በላይ በጠቀስነው ስእለታችን መሠረት የአውራጃው ለልዩ ልዩ ተግባር ወደ አዲስ አበባ የመጡትን ሰዎች የየአውራጃው የመሬት ሁኔታ እንዲያስረዱን ብንጠይቃቸው መልሱ በልዩ ልዩ ምክንያት እየታጠረ ነውነቱ ተሠወረብን ። ምክንያቶቹም የሚከተሉት ናቸው ፤

፩ — ቅናት ፤ ምቀኝነት ፤ ጥመት ።

፪ — በብዙ ሰዎች ላይ ደንበኛው የሀገር ፍቅር ስላላደረ ።

፫ — ከመምህራንም በኩል ከመዶ ሰማንያው ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት ስለሚሹ ስድብ እንጂ ምስጋናና ውበት አልተገኘም ።

መ ግ ብ ያ

ይህ መጽሐፍ የተጻፈበት ዋና ዓላማ የሀገሯን ልምላሜና ሀብት ቀኑጅናና ውበት በቅኔ ለመግለጥ መሆኑን በመቅድሙ ተረድተናዋል፡ በዚሁ መሠረት ከላይ እስከ ታች በቅኔ ስለሆነ አማርኛ ዐዋቂ ሁሉ በሰዋስው ግዕዛችን የተጻፉትን ዐሥራ ሦስት የቅኔ ዐይነቶች ከላጠና ጥልቅ ምሥጢሩን ከለመረዳቱ የተነሣ ፡ ሰምና ወርቁን ለይቶ ባለማ ወቁ ምስጋናው ስድብ ፡ ነቀፊታው ውዳሴ መስሎ መታየቱ የታመነ ነውና ቅኔ ሁለት ዐይነት ልሳን ያለው መሆኑን ተረድቶ ፡ ወደ ሂሱ ከመሮጥ በፊት በጥኋት አንጐል አስ ቸጋሪውን ሁሉ መላልሶ ማንበብ ያሻል ። በአዲስ አበባ ያልተለመዱ መስለው የታዩትን ቃላት በመጨረሻ በፊደል ተራቸው ከምዕላደ ቃላቱ ፍቻቸውን አንባቢ እንዲያገኘው ጽፈናል ። የጠቅላይ ግዛቶች ቅደም ተከተል በተሰየሙበት አባል ተራ ነው ። ራስ እጅ እግር እየተባለ የተሰየመበት ስም ጠቅላይ ግዛቱ በጣም አለው ተብሎ በሚጠራ በት ነው ። በደራሲው ዘንድ ከኢትዮጵያ አካላት ጠቅላይ ግዛቶች የሚበላለጥ የለም ፤ ሁሉም እኩል ነው ። ልምላሜና ውበት ግን የባለቅኔን አንጐል እንደከብት ማታለላ ቸው የታወቀ ስለሆነ ፡ ብዙ ዛፍና ሣር ፡ ወንዝና ጫካ ያለባቸው አውራጃዎች ከሌሎቹ ገነን ብለው ይታያሉ ። በዚህ መጽሐፍ የሰው ሥራ እንደ ጌጥ የውበት ማዳመቅያ ሁኖ ገብቷል እንጂ ፡ ዋነኛው የዛፍ ርዝመት ፡ ያዝመራና የከብት ሀብት ፡ የጫካ ልምላሜ ፡ የሣር አበቃቀል የወንዝ ብዛት ፡ የመሬት መዳበር ፡ የአየር መስማማት ፡ የውኃ ሙላት ፡ የሀይቅ ጥራት ፡ በንድ ቃል የሲሳይ ብዛት ነው ። ከዚህም በላይ አውራጃው የራሱን ግዳጅ አከናውኖ ወደ ውጭ ሊልከው የሚችለው ሀብት ነው እንጂ ፡ አንድና ሁለት ነገር ለባለሀገሩ የማይበቃ ወደ ገብያ የማይወጣ ከሆነ ዐይተን እንዳላየነ አልፈነዋልና አንባቢ ሁሉ ደራሲውን ከመንቀፉ በፊት ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን እንዲያስተውልና ተከታዩ እስኪወጣ ድረስ እንዲታገሠን እናሳስባለን ።

ከኰተኰቱት የማይለማና የማይለመልም መሬት በኢትዮጵያ አለመኖሩን ገምተን ፡ እንደ በሕር ዛፍ ያለውን ዘመን አመጣሽና ሰው ሠራሽ ልምላሜ ሐሳባችን የተፈጥሮ

ውበቷን ለመግለጥ ስለሆነ ትተነዋል ። እኛ ስንጐበኝ የጫከው ርዝራዥ ግንዱ ፡ ጉልጥ ምቱ ለጫካነቱ ማስረጃ ሁኖ የቄየንን በታ ግን እንዳለ ቄጥረን ጽፈነዋል ። ይህ መጽሐፍ መንግሥቱ ጥብቅ ሕግ አውጥቶ ደኑን በደንብ ከልጠበቀው ከ፵ና ከ፱ ዓመት በኋላ ጫካው ሁሉ ተመንጥሮ ፡ የተፈጥሮ ውበቷ ጠፍቶ ፡ በሰው ሠራሽ ጌጥ ስታጌጥ እኛ የደረስንባት ኢትዮጵያ እንዴት ያለች ለምለም እንደሆነች ያስረዳል የሚል እምነት ተጥሎበታል ።

ከላይ እንደተናገርነው ምንም የመጽሐፉ ዓላማ የሀገርዋን ውበት ለመግለጥ ቢሆንም ከሰው ሥራም በዙል የመሥሪያ ቤቱ መሪዎች ለመጐብኘት ከከለከ ሉንበቀር አብያተ ክርስቲያናት ፡ ትምህርት ቤቶች ፡ ሐኪም ቤቶች ፡ ታላላቅ ሕንፃዎች ይልቁንም እንደ ቅዱስ ላሊበላ ያሉት በሰፊው ተገልጸዋል ።

ቋ ን ቋ ፡

የምዕራበውያንን ሥልጣኔ ተከተልን የሚሉ ገጣሚዎች ሁሉ ፡ ገጣሚ ቋንቋን (ቃላት) እንደፈለገ ሊያሳጥር ሊያስረዝም ይችላል ይላሉ ። በሀገራችን ቅኔ ቤት ግን ቅኔ የቋንቋ ዘውድ ፡ የጥልቅ ሐሳብ መግለጫ ስለሆነ እንኳንስ ቃሉን ማወላገድ ይቅርና በወሬ የሚነገረው ተራው ንግግር እንኳ አይገባም ። ስለዚህ ባለ ቅኔ እንደ ፈለገ ቋንቋን ሊያጣምም አይችልም ፡ በቅኔው ውስጥ የሚጽፈውን ቃል ግን የሚናገረው ያንድ አውራጃ ወይም ወረዳ ሕዝብ ከተገኘ መላው ከላወቀ ተብሎ አይገደድም የሚለውን ጥንታዊ የቅኔ ሕግ ይዘን ሠርተንበታል ጥልቀ ምሥጢሩን ለመረዳት ቅኔ ፡ ጂዎግራፊ ታሪክ ዐዋቂ መሆን ያስፈልጋል ።

ዜ ማ ፡

በመጽሐፉ ውስጥ ፲፪ የዜማ ዐይነቶች ይገኙበታል ። ዜማው ሰበረ አልሰበረም ከማለት በፊት መላልሶ ማንበብ ያስፈልጋል ። ይልቁንም መወድሱ አማረኛ ስለሆነ የረዘመውን ጠቅሎ ያጠረውን አስረዝሞ ካላነበቡት የሰበረ መምሰሉ ስለማይቀር በጥንቃቄ ነጥቦችን ተከትሎ ፡ እንዲነበብ በጥብቅ እናሳስባለን ።

መ ግ ለ ጫ ፡

ከላይ እንደጠቀስነው የተሰየሙበትን አካል ተራ ቅደም ተከተል ይዘው ከዚህ በታች ጠቀላይ ግዛቶች ተጽፈዋል ። ሁሉም በአካል መመሰላቸው ግን ኢትዮጵያ የሁላችን አንድ ሰው ስትሆን ጠቅላይ ግዛቶቹ አካላትዋ መሆናቸውን ለማስረዳት ነው ።

አካል	ጠቅላይ ግዛት	
ጠጉር	ልምላሜ	ይህ የሁሉ ነው ።
ራስ	አዲስ አበባ	ዋና ከተማችን ስለ ሆነ
አንጐል	ሸዋ	መካሪና አስተዋይ አሳቢ
ዐይን	ትግሬ	መጀመሪያ ሕዝቡ በዚያ ስለገባ
ጆሮ	ኤርትራ	በር ስለሆነች
አንደበት	ጐጃም	ባለቅኔና ተናጋሪ ስለሆነ
ቃል	በጌምድር	ዜማዊ (የቤተ ክርስቲያን)
አንገት	ሲዳሞ	የአዶላ ወርቅ የሚታሠረው በአንገት ነው
ሽንጥና ወገብ	ኢሉባቦር	የዛፉና የአራዊቱ በጉንፍ መያዣ
ክንናድ	ወለጋ	የወርቅ አምባር ማሠሪያ
እጅ	ከፋ	የእደ ጥበብ መሥሪያ
ደረት	ሐረር	ስፋትና ፍራፍሬ
ልብ	ላስታ	በሕንፃ ላሊበላ ምክንያት
ጉልበት	ገሙ ጐፋ	መቀነት ጫካዋን የታጠቀችበት ።
እግር ቤት	አሩሲ	ላሚን የምታልብበት ።
መልክ	ወሎ	የሰው የመልክ ጥራት ።

ሀገራችን በአንስታይ መጠራቷ ውበት የሚገለጠው በሴት መሆኑና እናት በልጅዋ አለመጠርጠሯን ተገንዝበን ነው ።

ም ሕ ጻ ር ፡

ቅኔው የተጻፈው እናትና ልጅ እየተነጋገሩ ስለሆነ በናት ኢትዮጵያን ፡ በልጅ ደራሲውን እያሰቡ ነው የሚነበበው ። በምሕጻረ ቃል የሚነገሩት ቃላት ል-ልብ (ደራሲው) ኢ-ኢትዮጵያ መሆናቸውን ያስተውሏል ።

አጭር የቅኔ መግለጫ

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በቅኔ ስለሆነ፣ አማርኛና ግዕዝ ባወቅሽ ብዙ ቃላትም ባጠናሽ፣ አሰካኩን ካልተማሩ ቅኔ አይሰባምና ለማንኛቸውም አንባቢ ከለመረዳቱ የተነሣ ምስጋናው ነቀፋ መስሎ እንዳይታየው ለመጽሐፉ መርሕ የሚሆን ከዚህ ቀጥሎ (ያለውን አጭር መግለጫ ጽፈናል)። ከዚህ በታች ያለው የቅኔ መግለጫ ከሰዋስው ግዕዛችን የተጠቀሰ ነው።

ቅኔ፡

ቅኔ በሌላ ሀገር የማይገኝ፣ ግዕዝ ወልዶ አሳድጎ በሽምግልናው ለአማርኛ ያስተዋወቀው፣ በሰምና በወርቅ ተሸልሞ፣ በጎብር አሸብርቆ፣ በመንገድ አጊጦ፣ የደቂቀ ግዕዝን አንጐል ለማርከት፣ በደስታቸው ላይ ደስታ ለመጨመር፣ የልቡና ተድላ፣ የሕሊና ሐሤት፣ የአእምሮ ትፍሥሕት፣ የድካም መድኀኒት፣ የጎዘን ማሥረሻ፣ የቀኍን መውጫ፣ የፍልስፍና ማጐልመሻ፣ የልብ ማዳበሪያ፣ የዕውቀት ምርት፣ ጤፍ፣ ሥጋዊ ምግቧእን ደሆነች እሱም አእምሮአዊ ምግብ ሁኖ ከልዑል እግዚአብሔር ለኢትዮጵያውያን ብቻ የተሰጠ ሀብት ነው።

ልዩ ልዩ ልሳናት ስንማር ምንአልባት እሱን የመሰለ ጥበብ እንዳለ በማለት፣ በተቻለን መጠን ይልቁንም የግሪክንና የእንግሊዝን ባለቅኔ የሚባሉትን፣ ቅኔ ያላወቀ፣ ግዕዝን ያልተማረ፣ ሰምና ወርቅን ያላየ፣ ጎብርና ውስጠ ወይራን ያልሰማ፣ ስለምን የማይፈታ፣ መከዳ ያልተረዳ፣ የቋንቋችን እንግዳ፣ የጥበባችን ባዳ የሚያደንቀውንና የሚያገኘውን ግዋም ሁሉ ብናነብ፣ እንደ ኮረንቲ ሽቦ ተጠማምሮ እንደ ገመድ ተሸራርቦ የሚሄደውን የቅኔአችንን ምሥጢር አገኛለሁ ማለት፣ ከመሬት ቀኍጭ ብሎ በቀኝ እጅ ሰማይን ደግፎ በግራ እጅ ከዋክብትን መግፋት ሆነብን።

በንድ ቃል አስደናቂ ምትሐት (ሲኒማ) አስደሳች ትርኢት (ቲያትር) አስገራሚ ትዕይንት (ፊልም) ከማየት፣ ዳንስ ቤትም ገብቶ፣ ሳብ ርገብ ካለች፣ ወይኗ እንደ አዋቢያ ከከብ ከሚያበራና፣ እንደ መስተዋት ከሚፈልቅ፣ ወገብዋ የፈረስ ጭራ፣ ሽንሿ የመንፈቅ ጐዳና፣ በትዋ የተደፋ ኮልባ፣ ተረከዝዋ ክት፣ ኩማዋ ሎሚ፣ ዳሌዋ የገነነ ሽልባ ፍዋነቷ ዛር፣ ጣቷ የጉማሪ አለንጋ፣ አንገቷ ሞ ብርሌ፣ ደረቷ የቤተ ክርስቲያን ሳንቃ

ጫንቃዋ የቤተ መንግሥት በር ፡ ትክሻዋ ግርማ ሞገሷም ፡ ባሕሪዋ ርጉ ፡ ንቅሳቷ የሐር ዝምዝም ፡ ጥርሷ የወተት ዐረፋ ፡ ዐይን አገላለጧ የሰኔን ብልጭልጭታ ፡ ከንፈሯ ፍሕሶ ከመሰለ ሳዱላ ጋራ ሲደንሱና ሲጨፍሩ ከማምሽት ፡ በሰፈው ከተደገሰበትና ሁሉም ከተዘጋጀበት እዘመናይ ሀብታም በለጸጋ ሠርግ ሂዶ ፡ የጐጃሜን ዘፈን ከመስማትና እስክስታውንም ከመመልከት ፡ የምንጃሬን እንግጫ ፡ የጋላን ዳንኪራ ፡ የአምባሰልን ፡ ጭዋታ ፡ የትግሬን እምቧለሌ ከማየት ፡ የሱማሌን ለዘብታ ፡ የሸንቅላን እምቢልታ ፡ የአ ዝማሪን ግጥም ፡ ዘመናዊውን የፈረንጅ ሙዚቃ ከማዳመጥ ፡ የደባትሩን ወረብና ማኅ ሌተ ገምቦም ከመስማት ይልቅ ፤ ቅኔ ዐዋቂ የደስታ አክሊል ፡ የፍሥሐ ዘውድ የሆነ ውን በሰም ከውር የተቀረጸ ፡ በወርቅ የጠለቀ ምሥጢርን የተገነዳፈ ፡ በዘረፋ የነጠረ አንድ መወድስ ቢዘርፍ ወይንም ቢያነብ ፤ አንጐሉ ይታደሳል ፡ አእምሮው ይረካል ድካሙና ጎዘኑም ይረሳል ።

ከዚህ በላይ የጻፍነው አንባቢ ቅኔ በሌላ ሀገር ከሚገኙት ግጥሞች የተለየ ከፍ ያለ ምሥጢር ያለው ጥበብ መሆኑን እንዲረዳው ነው እንጂ ፡ የባዕድን ብልሐት ለማበጥ ለል ፡ ዕውቀቱን ለማቃለል ፡ ችሎታውን ለማራከስ ፡ ጥበቡን ለማኪያኬስ አይደለም ።

ግዕዝ የሰውን ሀገር ቅኔ የመሳሰሉ ጥሩ ጥሩ ግጥሞች መልክዕና ዐርኬ እንዳሉት ላማርኛም ዘመናዊ ተራ ግጥም ስላለው ቅኔ ግን የሁለቱ ቋንቋዎች የላይ ገንዘብ ነው ስንል ፡ ይህን ሐሳብ የሚቃወም ቢኖር ፡ የምዕራባውያን ሥነ ጽሑፍ ግዘት ቅኝ በመ ሆኑ ከእናት ሀገሩ ጥበብ አንዳችም ስላልቀሰመ ፡ የቅኔአችንን ስልትና መንገድ እንዳል ተረዳው በግልጥ ይታወቃል ።

በግዕዝና ባማርኛ በልዩ ልዩ ስልት ሲፈስ የኖረው ቅኔ ቢጻፍ ኑሮ ፡ በመላ ኢትዮ ጵያ ይልቁንም በጐጃምና በዋድላ ከዚያውም በዋሸራና በጐንጅ በሌሎችም የቅኔ መሪጌቶችና ሊቃውንት በሚገኙባቸው ታላላቅ አድባራት በአንድ ቀን ሌሊት ብቻ እንደ ክረምት ዝናም ያለማቋረጥ ሲወርድ የሚያድረው ቅኔ ብቻ ሽሕ ሽሕ ገጽ ያለው ዐሥራ ሰባት በሃያ አምስት ቢያንስ ስምንት ቅጽ ተከታታይ መጽሐፍ ይሆን ነበር ። ከዚህም በላይ በአማርኛ ከሴት ወይዘሮት ፡ ከወንድ መኳንንት ከገበሬው እስከ እረኛው ድረስ ሲፈስ የኖረው ስለምን ቢሰበሰብ ሥነ ጽሑፋችንን በጣም ያዳብረው እንደ ነበር የማይ ካድ ነው ።

አበቶቻችን የቅኔ ቋንጣ እያሉ ቢጥሉት ነው እንጂ ለወይን ያታክት ለአንባቢ ይሰለች ነበር ።

ምዕራባውያን ተናጋሪ ይማራል ፡ ባለቅኔ ግን ይወለዳል ይላሉ ፤ በእኛ ግን ማንኛቸ ውም ሰው ትጉህ ከሆነ ተምሮ ሊቀኝ ይችላል ። የቅኔ ተሰጥዎ እያለው ስልቱን ያል ተማረ ገጣሚ እንጂ ፡ ባለቅኔ ይሆናል ማለት ዘበት ነው ። ስለዚህ አንባቢ ሆይ ! በእየ ጊዜው በምንደርሰቸው መጻሕፍት ርዳታ ፡ ቢሆን እንድትቀኝ ፡ ያለበለዚያ እንደምንም ብለህ ቅኔ ብትሰማ ፡ የደስታህ ወሰን የሐሜትህ ዲካ እንደ ማይኖረው እያረጋገጥን ፡ የባ ዕድ ተጽዕኖ ለሌለበት ለንጹሑ ያባቶቻችን ሙያ መምሪያ የሚሆን መጀመሪያውን

መጽሐፍ በትሕትና ስናበረክትህ፡ መንፈሳዊ ቅንአት በተመላ ሂስ (ነቀፌታ) ስሕተታች ንን አርመህ፡ ያበቶችህን ጥበብ መሠረት ተከትለህ፡ አፋዊ ወጀቦ ያልነፈሰበት ቅኔ ጽ ፈህ፡ የሀገርህን ሥነ ጽሑፍ ታዳብራለህ በሚል ፍጹም ተስፋ ስለሆነ በቀና ልቡና ማለዳ ማለዳ መላልሰህ አንብበህ እንድትጠቀምበት አደራችን ጥብቅ ነው።

ቅኔ ምንድር ነው?

ቃሉ በሚሰጠው በቀጥተኛው ትርጉም ፍች ሳይሆን ገራገር አስመስለን ጥልቅ ምሥጢርን የምንገልጥበት ዘዴ የንግግር ስልት ሲሆን ሁለትና ሦስት ትርጉም ኑሮት ተጠማምሮ አንድ ሐሳብ ለመግለጥ የተነገረ እንደሆነ ቅኔ ይባለል። ይህንንም ስያሜ ለማግኘት የሚችለው ሰውዬው አስተካክሎና አከታትሎ የተናገረ እንደሆነ ነው። እንጂ በአጋጣሚ የዘባረቀውን ቅኔ ነው ብለን ብንከተለው ራሱ ተናጋሪው እንኳ እኛ ያሰብ ነው ፍች ስለማይገባው፡ በርግጥ ማሰቡን ሳንረዳ፡ ቅኔ ነው ተሰባን ብለን ልናመሰግ ነው ወይንም ልንነቅፈው አይገባም፡ በአማራው አውራጃ ሁሉ ፍሬ ደቂቅ፡ ሕፃን ልጂቅ፡ ወንድ ሴት፡ መኰንን ባላገር፡ ብልህ ገራገር፡ ጭዋ በዓለ እጅ ሳይለይ ስለ ሚሠራ በት ሲናገሩ ፣ ሲንጫጩ ወንጃ እንዳይለን ተጠንቅቀን ማጥናት ያስፈልገናል።

ደንበኛ አማርኛ ለመስማት ማንኛቸውም ሰው ቢያንስ ፲፪ የቅኔ ስልት ማወቅ አለ በት።

የቅኔ ዐይነት ፡

የቅኔ ዐይነት በጣም ብዙ ነው። ቅኔም የሚባለው በንግግሩ ስልት ነው እንጂ፡ ቤት በመታሸና ግጥም በገጠምሽ አይደለም። በቅኔ ዜማ ተሳክቶ ስልቱን ያልያዘ ግጥም እንጂ ቅኔ እንደማይባል ተራ ንግግርም ጎብርና ምርምር አንጻርና ሰም ለበስን የመሰለ ይዘ ሲገኝ፡ ቅኔ ነው።

ለቅኔ ሁሉ መሠረቱ ሰምና ወርቅ ነው፤ እሱም ተጣምረው አንቀጻቸውንና ቅጽ ላቸውን አንድ አድርገው እንዳንድ ባለቤት ተሳቢ ወይም ዘርፍ ሁነው በሚቈጠሩ ሁለት ስሞች ይመሠረታል።

የቅኔ ጸያፍ ፡

ሰምና ወርቅን በሰፊው ከመተንተናችን በፊት ቅኔን በቀላሉ ለመረዳት እንዲመ ቸን ጸያፎችን ከዚህ እንጽፋለን።

የሌሎች አህጉር ገጣሚዎች የግጥም መብት እያሉ ማንኛውንም ቃል ሊደነጉሩ ይልቀጉንም ሊያሳጥሩና ሊያስረዝሙ ይችላሉ። በግዕዝና በአማርኛ ግን ያላዋቂ ካልያ ዘው በቀር በስድ የሚጻፈው የንግግርና የሰዋስው ጸያፍ ሁሉ ክልክል ነው። የንግግር ጸያፍ የሚባለው በግዕዝ መልካም ስሜትና ፍች እያለው በአማርኛና በትግሬኛ መጥፎ ትርጓሜ ሲኖረው ነው። ምሳሌ እም ከሰና ከበ ጋራ ሲገናኝ፡ ግሙራ ነገራት፡ እም

ዳር ፡ አሮን ወዘተ ..... ።

የሰዋስው ጸያፎች ፡ አንድና ብዙ ፡ ሴትና ወንድ ፤ ቅርብና ሩቅ አይመሰሉም ምክ ንያቱም በአንቀጽ ስለማይገናኙ ነው ። ም. የጊዮርጊስ አንገት ላሞች ወተትን ታለቡ አይልም ፤ የጊዮርጊስ አንገት ላም ወተትን ታለበች ይላል እንጂ ። ለቀሩትም ችግሩ አሁን እንዳየነው ሁሉ ከማሠሪያ አንቀጽ ላይ እንደሆነ ያስተውሏል ።

ከላይ እንደ ጠቀስነው እንደፈተተውና በዘፈቀደ ሳይሆን የሚያገባውን ቃል ፡ ፈለ ጥ ፡ ዘዴ የሚሠሩበት የአንድ አውራጃ ሰዎች ከተገኙ ፡ ከነተረቱ አማርኛ እየቤቱ ነውና ጸያፍ ከልሆነ በቀር ባለቅኔው ነጻ ነው ። በዜማም በኩል ከግዕዙ ሥርዓት በቀር የአማ ርኛ ፲፱ ዐይነት ስላለው ባንዱ ቢሠራ ምርጫው የደራሲው ነው ። እኛም በዚህ ሕግ መሠረት በወል ዜማ ጊዜ የሚ የሚለውን አዛማጅ ቅጽል ሚ. ብለን ጽፈናል ምክንያቱም ሕዝቡ ስለ ሚሠራበት ነው ፤ ለምሳሌ የሚመጣ የሚሄድ በማለት ፈንታ ሚመጣ ማነው፡ ሚሄድ ማነው እያለ የሚናገረው ሕዝብ ምስክር ስለሆነ ጸያፍ አይባልም ። በዜማም በኩል ያማርኛ ሕግ ስለሆነ ያጠረውን አስረዝሞ የረዘመውን አሳጥሮ በማንበብ ፈንታ ብዙ ከተማ የማያውቃቸው ቃላት ስለ አሉ በንባብ ወቀበት ሲንገደገድ በእርጅና አለማ ወቅ ሲንቀጠቀጥ በአንባቢው ንዝህላል ምክንያት የተነሣ የሰበረ መስሎ ቢታየው መላ ልሶ እንዲያስተውለው አስቀድመን እናስጠነቅቃለን ።

በግዕዝ ከዚህ ያልተጻፉ ብዙ የቅኔ ጸያፎች አሉ ፤ ሁሉንም ለመረዳት ግን ሰዋስው ግዕዛችንን ይመለከቷል ። ግን ግዕዝን እንጂ አማርኛን ስለማይነኩ ከዚህ በላይ ያሉትን ለግዕዝ ቋንቋ ትተን ፡ ሰምና ወርቅ እንዴት እንደ ሚመሰሉና የፊተኛው ለኋለኛው ምንና ምን እንደ ሚተርፈው እንይ ።

በአማርኛ እንደ ግዕዙ ደንብ ከልተናበቡ በቀር ሰምና ወርቅ ፊትና ኋላ ሁነው ለመ መሰል ይችላሉ ፤ ም. ማርያም መፊት ክርስቶስ እኽልን አበቀለች ። መፊት ማርያም እኽልን ክርስቶስ አበቀለች ።

ሰምና ወርቅ ሲለዩም ፤

ሰም ፡ መፊት እኽልን አበቀለች ፡

ወ ር ቅ ፡ ማርያም ክርስቶስን ወለደች ፡ ይሏል ።

ሰም ለወርቅ ፭ ነገር ይተርፈዋል ፤

ምንና ምን ቢሉ ፤ አንቀጽ፡ ቅጽል ፡ ተናባቢ ፡ አፈታት፡ ዝርዝር ናቸው ፤ አገባብ ግን የጋራቸው ነው ። በሰም ወድቆ ለወርቅ በወርቅ ወድቆ ለሰም ይተርፋል ።

አተራረፉም እንደ ሚከተለው ነው ፤

አንቀጽ ሲተርፈው ፤

ወርቅ ይኳሻል ሰም ግን እውነቱን ብቻ ይተርካል ፤ ሰም ለወርቅ አምስት ነገር ለመ ትረፍ የቻለ ስለዚህ ነው ። አንቀጽ ነክ ዘለግለም የሰም ነው ፤ ወርቅን ቢመስል ግን ጸደቀ ይበላል ፤ ይህም ጸያፍ ነው ። አንቀጹን በሰም ገሥሦ በወርቅ አኳሽቶ ይፈቷል ፤

ይኸውም እውነቱን በሰም አንቀጽ ተናግሮ፣ ሰምና ወርቅ በሚለዩበት ጊዜ፣ የሰሙን አንቀጽ በመሰል ተክቶ ይፈቷል ማለት ነው። በንድ ቃል አንቀጹ በቀጥታ የሚናገር ለት ሰም ነው።

ም.(ሀ) ባልዋ በጋ ሙቷልና መበለት በለስ ልምላሜ ጌጧን ጣለች፡

ሰም፣ ባሏ ሙቷልና መበለት ጌጧን ጣለች።

ወርቅ በጋ አልፏልና በለስ ልምላሜዋን አጣች።

(ለ) ራምኖን ሳዱላ ውሽማዋ ክረምት ስለመጣ ጠጉርዋን ልምላሜ ከፈከፈች።

ሰም፣ ሳዱላ ውሽማዋ ስለመጣ ጠጉሯን ከፈከፈች።

ወርቅ፣ ራምኖን ክረምት ስለመጣ ለመለመች።

(ሐ) እናታችን ኢትዮጵያ በኃይለ ሥላሴ ፀሐይ በዘመነ መሳፍንት ሌሊት የጠፋውን ጥበብ ጌጧን ስላገኘች በጣም ደስ አላት።

ሰም፣ እናታችን ሌሊት የጠፋትን ጌጧን በፀሐይ ስላገኘች በጣም ደስ አላት።

ወርቅ፣ በዘመነ መሳፍንት የተቋረጠው ጥበቧ በኃይለ ሥላሴ ጊዜ ስለ ተመለሰላት ኢትዮጵያ በጣም ሠለጠነች።

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምሳሌያት ውስጥ ያሉት የሰም አናቅጽ፣ ጣለች፣ ከፈ ከፈች፣ ደስ አላት የሚሉት በወርቅ ጊዜ፣ አጣች ለመለመች ሠለጠነች ተብለው ሲፈቱ ሰም ለወርቅ በምን ሁኔታ አንቀጽ እንደተረፈው መላልሶ አንብቦ ልብ አድርጎ ይረዳል።

ቅጽልም ፣ ያንቀጽ ስሜት ስላለው ከዚህ በላይ የጠቀስነውን አፈታት ይከተላል፤

ም. በጋ አጋሚዶ ጠጉር ልምላሜዋን የላጫት ቄንጆ ራምኖን ኩምሽሽ አለች።

ሰም፣ አጋሚዶ ጠጉሯን የላጫት ቄንጆ ኩምሽሽ አለች።

ወርቅ፣ በጋ ልምላሜዋን ያጠወለገባት ራምኖን ደረቀች።

ተናባቢ፣ ይህ በግዕዝ ነው። በአማርኛም ተዛራፊን ይመስላል፤ ም. የእንባ ሙላ ት ወሰደው፣ የኀዘን ሞገድ አሰጠመው። የችጋር ባሕር ዋጠው ወዘተ ....።

አፈታት ሰሙን ለመከተል ሲል የተጣመመውን ሐሳብ አቃንቶ መፍታት ነው።

ይህንም ለመረዳት አንቀጽ በሚለው ምሳሌ የሰጠነውን እንደገና ይመለከቷል።

ዝርዝር፣ ለዜማ ቦታ ካልቸገረ በቀር ሁልጊዜም በሰም ሲዘረዘር ያምራል። ይኸ ውም አገናዛቢ ቅጽል ከሰሙ ስም ላይ ይዋል ማለት ነው።

ም.(ሀ) በነገር ጦሩ ወጋው፤

ሰም፣ በጦሩ ወጋው

ወርቅ፣ በነገር ነካው

(ለ) ጸደይ ሙሽራ ነጭ ልብሷን ተጐናጽፋ ወጣች።

ሰም፣ ሙሽራ ነጭ ልብሷን ተጐናጽፋ ወጣች።

ወርቅ፡ በጸደይ ነጭ አበባ ይበዛል ። አገባብ ግን ለሁሉም ነው ። ይህም ባሁኑ አነጋገር መስተዋድድና መስተፃምር የሚባለው ነው ። ም. ጳውሎስ በሰይፉ ትም ህርት ዓለምን አቀና ።

ሰም፡ ጳውሎስ በሰይፉ ዓለምን አቀና ።

ወርቅ፡ ጳውሎስ በትምህርቱ ዓለምን አሳመነ ። ሰም ለወርቅ የሚተርፋቸውን ነገሮች ካሳየነ ምንነታቸውን ደግሞ ከዚህ በታች እንገልጣለን ። ሰም የሚባለው ቃል የመጣ ከንጥረኛ ከውር ነው ። አንጥረኛ የሚፈልገውን የወርቅ ወይም የብር ጌጥ፡ መጀመሪያ በሰም ምስል ላይ ቀርጾ ወርቁን አቅልጦ ይደፋበትና ከረጋ በኋላ ወርቁ የሰሙን ቅርጽ ይዘ ይነሣል ። ስለዚህ ሰም ፡ ወርቅ በቅኔ ከውር ውስጥ የሚሸፈንበት ቤት ስለሆነ የወርቅ አምሳል መርገፍ ነው ። ወርቅ ከሰም ጋር በተ ነገረ ጊዜ የኋለኛውን ልብስ ለብሶ መታየት ሲኖርበት በተለየ ጊዜ ግን ራሱን ችሎ እንዲያብረቀርቅ መወልወል አለበት። ሰምና ወርቅ እንደ አህያ ጆሮ እኩል ስለሆኑ በሰም በኩል በየራሳቸው ወገናቸውን ማቅረብ አለባቸው ። ሰምና ወርቅ ባልና ምሽት ስለሆኑ ጋብቻቸውም እንደ ጐጃምና በጌምድር ባህል ነው ማለት ነው። ይኸውም የግራ ቀኙ ወላጆች በሚሰጡት ቱለት ተስማምተው አንደኛው ወሥር ወሥራ-አምስት ከብት ቢያመጣ ያኛውም ተቃራኒው ያመጣውን ያህል ማቅረብ አለበት ፤ ማጫም እንኳ ቢሰጥ ዕጥፍ ሁኖ በሙሽራው ሽልማት ጊዜ እንደሚ መለስ ብናስተውል ሰምና ወርቅን በቀላሉ ልንረዳቸው እንችላልን ። ሁለቱም በዚህ ወይነት የጋብቻቸውን ሥርዓት ፈጽመው ቅኔ የሚባለውን ቤት ሠርተው አቶ ኅብርን ወልደው ፡ ንብረት ሥነ ጽሑፋቸውን አስፋፍተው እንደሚኖሩ በሚከትሉት ምሳሌዎች እናስረዳለን ።

ም.(ሀ) ጥበበኛ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያ ልብስን ሰፋ ።

ሰም፡ ጥበበኛ ልብስን ሰፋ (ይህ እውነት መሆኑን ይመለከቷል) ።

ወርቅ፡ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አገናኘ (ኳሸ)

(ለ) አንበሳ ምኒልክ ጣሊያን ተኩላን ሰበረ ።

ሰም፡ አንበሳ ተኩላን ሰበረ (ተረክ)

ወርቅ፡ ምኒልክ ጣሊያንን አሸነፈ (ኳሸ)

(ሐ) ኃይለ ሥላሴ ሥልጣኔ መብራትን አበራ ።

ሰም ፡ ኃይለ ሥላሴ መብራትን አበራ ። (ተረክ)

ወርቅ ፡ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣኔን አስፋፋ (ኳሸ)

(መ) ገበያተኛ ተማሪ በተማሪ ቤት ገበያ ዕውቀት ዋጋን ይገበያል ።

ሰም ፡ ገበያተኛ በገበያ ዋጋን ይገበያል (ታሪክ)

ወርቅ ፡ ተማሪ በተማሪ ቤት ዕውቀትን ይማራል (ኵሸት)

(ሠ) ከተሜ ወሬ እኽልን ይሸምታል ።

ሰም ፡ ከተሜ እኽልን ይሸምታል (ታሪክ)
ወርቅ ፡ ከተሜ ወሬ ይፈልጋል (ሹሸት)
ከዚህ በታች ያለውን መልመጃ በተሰጠው ሕግና ምሳሌ መሠረት ይፈቷል ።

፩ በአንደበት እጁ ምስጋና ከበሮን ይመታል ።
፪ በአእምሮ እግሩ ሂዶ ዕውቀት እጓቱን ጐበኘ ።
፫ ሀገራችን ባልቴት በህል ኩታዋን ጥላ የምዕራብን ልጅ ሥልጣኔ ከነንፍጡ ጉድለት ታቅፋ ሰመችው ።
፬ ላጭ መለኛ ሰውን በነገር ምላጭ ይላጫል ።
፭ ደመና ሰው በመብረቅ ጥርሱ ይስቃል ።
፮ ጨረቃ አንጐል በሐሳብ ምሕዋር ዓለምን ትዘራለች ።
፯ ስካር ገነኛ በሰው እሩር ራስ ይጫወታል ።
፰ አሳላፊ ደዌ ሰው ድግስን በሞት ጥዋ እየገለበጠ ለተጋባዥ መቃብር ያድላል ።
፱ ልደት ጦረኛ ሞት ጠላቱን ጠንክሮ ይዋጋል ።
፲ መንገደኛ ጻድቅ በሞት ድልድይ ይህን ዓለም ወንዝ ተሻግሮ መንግሥተ ሰማይ ሀገሩን ይገባል ።
፲፩ በሙዚቃ በንዚን አንጐል መኪናን አስነሣ ።
፲፪ እረኛ ንጉሥ ሕዝብ ከብቱን ይጠብቃል ።
፲፫ ገበሬ አባት ልጅ ተጋኑን ይኰተኵታል ።
፲፬ ብልግና አረም የበላው አዝመራ ልጅ ፍሬ ምግባርን አያፈራም ።
፲፭ ውዳሴ ከንቱ መርዝ የሞኝ አይጥ መግደያ ነው ።
፲፮ ከተሜ ተራ ግጥም ጐመንን ቸብሰ ማር ቅኔን ቢያቀርቡለት አንጐል ሆዴ ሞላ አለ ።
፲፯ ትዕቢት የውኃ ሙላት ዋናተኛ ትዕቢተኛን ያዋርዳል ።
፲፰ ሰይፍ ትሕትናን የታጠቀ ጠላት ትዕቢትን ቁረጠ ።
፲፱ ዛፍ ሰው ቅጠል ልብስን ለበሰ ።
፳ ዳኛ ሚዛን ከለል ጉቦ ወዳለበት ያዘነብላል ።
፳፩ ንብ ተማሪ አበባ ዕውቀትን ይቀስማል ።
፳፪ ጀግና አቶ ዕውቀት ጠላቱ ድንቁርናን በጠብመንጃ ትምህርት ተመልሶ እንዳይ መጣ አምሎ አባረረው ።
፳፫ በወይኑ ልብ ዕውቀት ዓለምን እየዘረ አየ ።
፳፬ ወምበዴ በጋ የገፈፋትን መንገደኛ ራምኖን በለጸጋ ክረምት ልብስ ልምላሜን ስላለበሳት ቅጠል ጠጕሯን ከፍክፋ ብቅ አለች ።
፳፭ በመከራ ጅራፍ ተገረፈ ።
፳፮ በእሳት ምላስ ሀገር ሕዝብን አቃጠለ ።
፳፯ በክሰል ነገር ነጭ ልብሱን ልብ ሞገሞገበት ።

፷፰ የክርስቶስ ፍቅር እሳት የመናኒን ልቡና ዱር ያቃጥላል ።

፷፱ መምህር ገበሬ የተማሪን ማሳ ልብ በማረሻ ትምህርት አርሶ ዕውቀት እኽልን ይዘራል ።

፸ በመላ እጁ ወተት ሀገርን ሰበቀ ።
በግጥምም ሲገባ እንደ ሚከተለው ነው ፣

ስለ ዐቢይ ጾም ፡

በዐቢይ ጾም ጥሉላትን ትተው በሕጉያን የሚበሉት ሣር ቅጠል ስለሆነ ከዚህ በታች ለአሉት ቅኔዎች ወርቅ እሱ ነው ። እነሱም በእየጊዜው ለመማሪያና ለማስ ተማሪያ የተሰጡ ናቸው ።

(ሀ) የሆድ ፋኖ ብሎት አምላክን ማይፈራው ።
ጥሉላት ድኖችን ሲያስጨንቃቸው ።
ዘበኛ ዓቢይ ጾም ደርሶ አዳናቸው ።

ለ) እድናለሁ ብሎ ከሆድ የሚያሠጋ ።
ከቢይ ጾም በላባት ሩጦ ተጠጋ ።
የወተት ጓደኛ አቶ ፈሪ ሥጋ ።

(ሐ) እንዲያመልጥ ረዳህ አልዓዛር እሥረኛን ።
ብሎ ወህኒ አዛዥ ሞት ቢያሥረው ክርስቶስን ።
ይግረምህ አለና አፍርሶለት ሄደ ወህኒ መቃብርን ።
ተደፍሮ ማያውቀው ወህኒ መቃብር ።
በእሥረኛ ክርስቶስ ትላንት ቢሠበር ።
በዓለም ከተማዎች ሆነ ድንጉርጉር ።

(መ) ጀግናው ዐቢይ ጾም ቢታይ ብቅ ብሎ ።
ቅቤ ፈረጠጠ ሀገር ድስቱን ጥሎ ።

(ሠ) ምስጋና ግብርን እየሰበሰበ ፣
ንጉሡ ክርስቶስ ካገሩ ቀረበ ።
ንጉሥ ክርስቶስን እያሞጋገሱ
ዘንበቦች አዝማሮች ቀርበው እጅ ነሡ ።
ይህ ብቻ አልነበረም የቀረበለት
ይጠብቀው ነበር የመከር ዐሥራት ።

(ረ) ቢትወደድ ፋሲካ ቤተ ዘመድ ጋብዘው
ጥሉላት ወገኖች በሙሉ ተጠርተው
በሰቃቴ አዳራሽ ሁሉም ተሰብስበው
እሳት አሳላፊ ሲያስተናግዳቸው

በጣም ደነገጡ ሆድ ቡዳ ቢያያቸው ።

(ሰ) መንግሥት ግብር አግብቶ ዮሐንስ ሲያበላ ፡
የኢጣልያን ወታደር በምጥዋ ቄላ
እጅግ ተሠቃየ በጣሙን ተጉላላ
አላስገባው ብሎ በረኛው አሉላ ።

(ቀ) ከብት እንዳያጠፉ ያውሮጳ አራዊት
እረኛው አሉላ በታላቅ ንቃት
ተግቶ ይጠብቃል ቀንና ሌሊት
ስለ ጥቢ ፡

(በ) ነጭ አበባ መስላ ሙሽራ ጸደይ ፡
ከክረምት አዳራሽ ለሰው ልትታይ
ብቅ ስትል ጊዜ በጽጌ ደባይ
አ ብ ታ ሳዱላ በጣሙን ሳቀች
መስክ አበባ ጋሜ ተንከተከተች
አመንዝራ ቀጋ ጥርሷን አሚጨች
ወይዘሮ ወይኒቱ ልብሷን አጠበች
እጎቷ በለስም ቅቤ ተቀባች
ለሠርጉ ሲመጣ በጋን ስላየች ።
አደይ ልጃ ገረድ ቀይ ሹራብ ደርባ
ታጨበጭባለች በእጅዋ እምቡጥ አበባ
ተሸኰረመ መማለች አድዮ ኰረዳ
ጠቅሷት ስላለፈ አበባው እንግዳ ፡
ይህንም ሁላ ዐይታ ቄንጆ ጽጌ ረዳ
በአበባ ሳቅ ልትሞት ልቧ እስኪፈነዳ ።

የደራሲው ደቀ መዝሙር ዮሐንስ አድማሱ በ፲፱፻፺፪ ዓ. ም. ለቅኔ ውድድር በዩኒ ቬርስቲ ኮሌጅ የተናገረው ቅኔ ሰምና ወርቅ ስለሆነ ከዚህ ቀጥለን ጽፈነዋል ።

ዘመነ ክረምት ።

ዕድገትን ልምላሜ ለሚያመጣው ጌታ ፡
ለታደለው ክረምት እጅግ ለበረታ
እጅ መንሻ ሚሆነው የመታያ አምጓ
እነሆ አቀርባለሁ የቅኔ በተጓ ።
ጌታው አቶ ክረምት ድግስ ደገሰና
አስጣለ በሰፊው ድንኳኑን ደመና ፡

ዝናም ጠላ ጠምቆ በነጐድጓድ ጋን
በውሽንፍር ሳሌ ጥሎ ኂል ጠጅን
ሹሞ አስቀመጠና ወጨፎን ፊንቄን
ይናኘው ጀመረ በከልባ እርክፍክፎ
ለዕፀዋት እንግዶች በወጉ አሳልፎ ።
ጌታው አቶ ክረምት ነፋስ ገረዱን
እንድ-ትሠራ አዘዛት ወጦች አትክልትን
አዛኸር ናዛኸር አርነም ለቀቀ ሁሉን ፣
አዋዜ ጭጋግን መጥና አሰምራ
ጉም ቅቤን አምቃ በማሠሮ ጋራ
ወተት ዋግን ይዛ በሰቢያ ቅምጫና
ልትሠራ ተነሣች ለሕይወት ለጤና ፣
ጉዝጉዝ መብረቅን ሁሉን በያይነቱ
ዳበ ብልጭልጭታን ለሚፈልጉቱ ፣
ልትጋገር ታጠቀች በሰማይ ምጣድ
ዕንጨት ጮቅን ማግዳ እሳት ልታነድ
እሳቱም ጎይለኛ እስከ ስሙም ብርድ
ምንቸት አብሽ ዋግን በድስት ጤዛ ጥዳ
ሙያዋን አሳየች ለዚያ ሁሉ እንግዳ ።
ዕፀዋት ወይዘሮት የሚያምረውን ልብስ
አጥልቀው መጡና ልምላሜን ቀሚስ
በጣም ተደሰቱ በዚሁ ድግስ
በወግ ተጠፍሮ በረዶው ከበሮ
ይዘፈን ነበረ ሁሉም ነገር አምሮ
ከሁሉም ከሁሉ ከሁሉም ይልቅ ፡
ከእንግዶቹ ሁሉ የሆነችው ድንቅ
ኰረዳ ራምኖን በጣም ያማረች
ወሰው በሏን ክረምት እጅግ የሰየች
ይህች ኰረዳ ራሷን ከፍክፋ
ጥልፍ ቀሚስ ቅጠሏን በጣም አንዘርፍፋ
ተኵላ ተቀብታ እጅግ አሸብርቃ
ጥንግ ድርብ ልምላሜን ደርባ እጅግ ደምቃ
ጭቃ መጫሚያንም ተጫምቃ በውል ፡
በጐርፍ ስጋጃ ላይ ዅብ ዅብ ስትል ፣
አማቂጠን ገረድ እንግጫ ሎሌን

ብትገባ አስከትላ ደመና ድንኳን፣
ዕፀዋት እንግዶች ተነሡ በሙሉ
ጌታው አቶ ክረምት ቆመና እንዳመሉ
የራምኖን ሚስቱን እጅ ቅጠሏን ይዘ
አኖራት እጮኑ ውራን ጨርቅ ጐዝጉዘ።
ከዚያማ በኋላ ሁሉም ተፎለሉ
እውነተኛ ገነት እስኪመስል በሙሉ።
መቼም በዚህ ዓለም ሁሉ እኩል አይደላው
አንዱ ሲንደላቀቅ ሲቸግረው ሌላው
አንዱ ከፍ ብሎ አንዱ ዝቅ ሲል
ጊዜው ይሄድና ዘመኑ ያልፋል
የኑሮ አመሳሰሉ እንዲህ ያጉላላል
ወይዘሮ ወይኒቱ ቢሞት ባሏ በጋ
ጥንግ ድርብ ልምላሜን ትታው ጣል አድርጋ
ድርቀት ማቅን ለብሳ መርገፍ ቀልቤን አሥራ
ታለቅስ ነበረች በጣሙን አምርራ።
ከድግሱም በራፍ ስታስተውል ቁማ
መሰለች ለሁሉም የሆነች ደለማ።
እኅቷ በለስም ቅጠል ዐይኗ ቀልቶ
ልታጥናናት መጣች ምን ሊረባት ከቶ
በለቆ ሽክና ዝናም ጠላን ይዘው
ሲለጉትም ጊዜ መልሰው መልሰው
ሥራቸውን ናላ በፍጹም አዘረው።
ራምኖን ዘብል ይህንን ጉድ ዐይታ
ሽንጥ ቅጠሏን ይዛ ወጣች ለቻቻታ
ታወራ ጀመረች ዕድገትን ተረት
ስለባሏ ታሪክ ስላቶ ክረምት፣
እናንተ በልቴቶች ስሙኝ ልንገራችሁ
ግብራችሁ ያረሚ ሥርዓት ያልገባችሁ።
አንድ ባል ለሁለት ሕግን ሳታከብሩ
ያለ ዕፍረትም በግልጥ ይዛችሁ ምትኖሩ
እንኳን የደም ልቅሶ ፊትን ሳምባ አድርጎ
ማድረግ መቀጣጫ አንድ ሕግ ደንግጎ
ይገባ ነበረ፣ ብቻ እንሥራ በጎ።
ግና ምን ይሆናል ስንቱን ይቈጧል

በማስለቀስ ብቻ ማለፍ ይገባል ፣
እኔ ግን ምታዩኝ እንደዚህ አምሬ
ሽጋ ባሌን ክረምት በጣሙን አክብሬ
እኖራለሁ በሕግ ይኸው እስከ ዛሬ
እስቲ ተመልከቱት በወግ በሥራት
የጅሬን አበዛዝ የክብሬን ብዛት ፣
የኔ ባል ደግ ነው እጅግ በጣም ቸር
እንኳን እኔን ምሽቱን ሌላውን ሳይቀር
ያሸሞነሙነዋል በልምላሜ ሐር ።
ግና የናንተ ባል በቁም ቀበራችሁ
ረጀትም ሳይተው እንዲያ የጠፋችሁ ፣
ለኔማ ጠላቴ የዛሬ ባላንጣ
አንድ ጊዜ ይቅርና እውነትስ ቢወጣ
ሁለት ጊዜም ቢሞት አይለኝም ቅር
ዓለሜ ነውና የእሱ ሞት በምር ።
በሰኔ ታጭቼ በሐምሌ ተድሬ
በነሐሴ ጫጉላ በጣሙን አምሬ
በአፍላዬ እከርማለሁ በደንብ ተክብሬ
መዋኔውን ይስጣችሁ እግዜር ያዋናችሁ
በእያመቱ እልቅሶ ለሚያገኛችሁ
በአበቃችም ጊዜ ይህንን ተናግሬ
አቶ ክረምት ባልዋ ቀጠለ በተራ ፣
ያቶ በጋን ጎጢአት በይፋ ሊዘራ
እኔ እኮ አቶ ክረምት አላደላ ከቶ
እንኳን ምወደውን ማፈቅረውን ቀርቶ
ማልበሱን ወውቃለሁ ሁሉንም አካቶ ።
ሰው መቸስ ከምሽቱ ማን ይቀርበዋል
ያለውንስ ከሷ ምን ይሠውራል
ከመሠወር በላይ ማስለቀሱስ ደግሞ
የክፋት አበጋዝ የአረሚ ፈጽሞ
እስቲ ተመልከቱት የኔን ልግስና
ሁሉን አስገባና በድንኳን ደመና
አጠጣቸዋለሁ እስኪንጀባረሩ
እስኪ ሞቀው ድረስ የእንግዳው አውታሩ
ብትመለከቷት ብታይዋት ምሽቴን

የፊቷን ወረራ ያቀማመጧን
በአጭሩ ልታውቁት ትችላላችሁ
የኔን ለሷ ማሰብ ከዚህ ቁማችሁ
ታሪክ አላበዛም ልተወው በጭሩ
የባላችሁ ክፋት ሚሆን ምስክሩ
የእናንት ሁኔታ ነው አድርጎ በጥሩ
ወይ ሰውና በለስ መከራ ክረምት
ሲመጣ መንጫጫት ሲሄድ መደሰት
ምሽቲቱ በተራ ባልዮው በተራ ተናግረው ሲያበቁ
እንግዶቹ ሁሉ በጣም ተደነቁ።
ይህንን ሲሰሙ ወይንና በለስ
ጎዘናቸው በዛ ከፊቱ ይብስ
ይህንን ንግግር የዘለፋ መዓት
አፍ እንደሌለው ሰው በታላቅ ትዕግሥት
ተቀብለው ሄዱ እጅግ በመፍራት።
ቀን የጣለውን ሰው ቀን እስኪያነሣው
ምን ምን ሳይሉ እንዲያው ዝም ነው።
ግን የኮለጁ ወጣቶች በእንግሊዝኛ እንጂ በማርኛ የገፋ ስላልነበሩ የሚሰማው ስላጣ የሚከተለውን እንጉርጉሮ ተቀኝቷል።
ሳላውቅ አጠፋሁ ጥፋት
እንዲያው አንድ ቀን ድንገት
አበባ ቅኔን መልከም ልጇ
በኮሌጅ በረኻ ሰድጇ
ያንን በረኻ ሊያቀና
ከንበል ደፋ ሲል ዋለና
የቀትር እባብ ድንቁርና
ነድፎ ገደለው ትላንትና
ግና ቢሆንም ደግሞ
ምንም አላዝንም ፈጽሞ
በዕለተ ምጽአት ዕውቀት
ኋላ ይነሣል በውነት
ከኮሌጅ ሰማይ ድንገት
ምንም ሳይታሰብ አንድ ዕለት
ቅኔዬ ብራቅ ቢበርቅ
ያን ጊዜ ሆነ ድብልቅልቅ

ምን ሆነ ብዬ ሳሰላ
ትልቅ ጉድ ኑሯል በዚያ ሁላ
ኰርማ ተማሪ የሚዳው
በጣም ወገሸ ቢያየው ።
ከዚህ በታች ያሉት ከዘፈንና ከእንጉርጉሮ የተሰበሰቡ ናቸው ።
ወይ አልተቈጣሁት ወይ አልመታሁት
አእሮፕላን ልቤ ሲሄድ አየሁት
(ሀ) አእሮፕላን ልቤ ሄደ ገሠገሠ
ወይኔ በሰንፍናው ቀረ እያለቀሰ
(ለ) ዕፀ በለስ በልታ ሔዋን ከንፈርሽ
መድኀኔ ዓለም ልቤ ተሰቀለልሽ
(ሐ) አላሠራሽም ወይ መዝጊያ ለቤትሽ
ወለል ብሎ ታየኝ ሣንቃው ደረትሽ።
(መ) የእግር ውኃ አሙቄ በርገሬ ሳልቄየው
ሞት እንግዳ መጣ እረግ ወዬው ወዬው ።
(ሠ) ከቤት እንዳልወጣ ርቄ እንዳ ልሄድ ፣
ተብትበህ አሠርሽኝ በፍቅር ገመድ ።
(ረ) ሽማግሌው በሬ ላይላዩን እለፍ
ወይፈን ይወጋሃል ስትንቀረፈፍ
(ሰ) ከንፈርሽ ብርቱካን እንዴት ጥሩ ነው
ሲመጡት ቢውሉ ማይጠገበው ።
(ቀ) አንቺ ያገሬ ቄስ እኔን መጽሐፍሽ
ጥኋትና ማታ ትደግሚኛለሽ ።
(በ) ጊዜው አለፈብኝ ተረሣኝ ሥራው
ከፊቴ ተሰቅሎ ትዝታህ ፎቶው
(ተ) ከፊቴ ተሰቅሎ ስላስቸገረኝ
ትዝታ ፎቶህን መዋተህ አንሣልኝ
በእየንኡስ ሐረጉ የሰምና ወርቅ ስሜት የያዘ ድርሰት ፣

ጸ ደ ይ ፡

በሐምሌና በነሐሴ ሰማይ አጋሚዶ ፊቱን በደመና ክሰል አጥቍሮ ፣ መዓት ዝናም ቀጣውን እያወረደ ፣ ዓለሙን በወጨፎ ሲያስጨንቀው ፣ በወጀቦ ጅራፍ ሲገርፈው በበረዶ ነገር ሲመታው ፣ በውሽንፍር ጥያቄ ሲያዋክበው ፣ በጉም ጨርቅ ዐይኑን ሸፍኖ ሲያደናግረው ፣ የነበረው ጀገጀጉና ጨለማው ዘመነ ክረምት አልፎ ፣ ወጣት ጸደይ ልምላሜ ኩታን ተደቡኖ ፣ ዳዋ ጋቢን ተጐንበ ፣ ሣር አግዳሚን ተጐናጽፎ ፣ አበባ ዘውድን

ተቀዳጅቶ፡ በጎብረ ጽጌያት አሸብርቆ ብቅ ሲል፡ መላዋ ፍጥረት ሙሽራ እንዳየ ሠር ገኛ በፍሥሐ ተውጣ በደስታ ትፈነዳለች። በዚህ ወራት መሬቱ ምጥጥ ሲል፡ ጓሳው ሲውለበለብ፡ አዝመራው ሲዘረዝር፡ ሣር ቅጠሉ ሲለመልም ነገደ ዕፀዋት ሲያብቡ፡ ወደ ተራራ ቢወጡ፡ ዓለሙ ሁሉ የመስቀል ደሽ የተተኰሰበት መስሎ ሲያብረቀርቅ ይታ ያል። በየሸለቆውም በእየሜዳው ያለው ግጫ ከዘመናዊው ፍራሽ እኔ አበልጣለሁና ተኝቸኝ እያለ የሰውን ልብ ሲያባብል፡ ጨፈው ደግሞ ኑ ተንከባለሉብኝ ተምበልበሉ ብኝ እያለ ያለፈ ያገደመውን ሕሊና ይማርከል፤ አእምሮን ያነሆልላል። በእየሸንተረሩ የሚተርና የበቁላ እንዙቶአቸውን ቅመው፡ የገብስ የስንዴ የጠመኸር እሸታቸውን በል ተው፡ የጊደር ወተታቸውን ገልብጠው ጐረምሶች ሲያቅራሩና ሲፈክሩ፡ ፍራፍሬውን ለቅመው የጠራ ውኃ ጠጥተው አዕዋፍ ሲበሩ፡ ጎይለኛ ጀግና የወነጨፈው ምድር ነጐድ መስለው ጥሩውን ሰማይ እየቀደዱ ሲወረወሩ ያየና ያስተዋለ ተመልካች ሁሉ ከደስታው ብዛት የተነሣ ሳይጠጣ ይረክል፡ ሳይበላ ይጠግባል። በንድ ቃል ጨለማውን ክረምት አሳልፎ፡ ብርሃን ተጐናጽፎ አበባ ተክናንበ፡ ጥጋብን ይዘ መክር መድረሱን እያበሠረ አቶ ጥቢ ከተፍ ሲል በመምጣቱ ልቡናው የሚይደሰት፡ ሕሊናው የሚይፈነ ድቅ አእምሮአዊ ፍጥረት የለም።

፪ ጎብር፡

ለሰምና ለወርቅ ያላንዳች አድልዎ የሚያስተባብር ስም በቅኔው ውስጥ ሲገኝ ጎብ ር ይበላል፤ ይኸውም የጎብረት የጋራ ማለት ነው፤ ሰምና ወርቅ ሲለዩ ለሁለቱም የሚ ደርስ ቃል መሆን አለበት። ሰምና ወርቅ ባልና ሚስት ሲሆኑ ጎብር ልጅ ማለት ነው። አጎበረ አስተባበረ ከለው ቃል የመጣ ስለሆነ በጎብርነት የሚገባው ስም ትርጉም ያላን ዳች ምርምርና አድልዎ ለግራ ቀኙም እኩል መሆን አለበት፤ ትርጉሙ በቀጥታ ከለ መፈታቱ የተነሣ ወዳንዱ ያደላ እንደሆነ ምርምር እንጂ ጎብር አይበልም።

በቅኔ ቤት ለጌታና ለእመቤታችን በጎብርነት የሚያገለግሉት ቃላት ከዚህ በታች የተጻፉት ናቸው።

እመቤታችን፡	ጌታ፡
ፈለግ	ማይ
ሰማይ	ፀሐይ
መሬት	ደብር
ደብር	ዕብን
እናት	ልጅ
እም	ወልድ
ገዳም	አንበሳ
ደመና	ዝናም

ዕፅ	ፍሬ
መርዓት	መርዓዊ
ጽርሕ	ንጉሥ
ሐይመት	ልዑል
ንግሥት	ንጉሥ
መሶብ	ኅብስት ወዘተ...

ለስድ ንባብ የሚከተለውን አብነት ይመለከቷል ።

(ሀ) ነገር ወጥን በምላሱ ላሰ ።
ሰም ፡ ወጥን በምላሱ ላሰ ።
ወርቅ ፡ ነገርን በምላሱ ቀባጠረ ።

(ለ) ዕረፍት የለሽ ነጋዴ ተማሪ ገንዘብ ማሥመረያን በእጁ ጨበጠ።
ሰም ፡ ዕረፍት የለሽ ነጋዴ ገንዘብን በእጁ ጨበጠ ።
ወርቅ ፡ ዕረፍት የለሽ ተማሪ እጁን በማሥመሪያ ተመታ ።

(ሐ) በዓል ትምህርትን የሚያከብር ተማሪ ጥበብ ለብሶ ወጣ ።
ሰም ፡ በዓልን የሚያከብር ተማሪ ጥበብ ለብሶ ወጣ ።
ወርቅ ፡ ትምህርትን የሚማር ተማሪ ጥበብን ይገበያል ።

(መ) በዓል የማያከብር ሴት ሕግ አፍራሽ ናት ።
በተሰጠው አብነት መሠረት ከዚህ በታች ያሉትን ምሳሌያት ይሠነጥቋል ።

፩ የጳሎውስ አክስት ሰይፍ የጊዮርጊስን አንገት ሳመች ።

፪ ጎይለኛ ጳውሎስ በንገቱ የተሸከመውን ሸክም ሰይፍ ቶማስ መጣና በእጁ ብድግ አደረገው ።

፫ ቂርቆስ ምስክር ችንካር ነገርን በዐይኑ አይቶ በጆሮው ሰምቶ ለነፍሱ ሲል መሰከረ ።
በዜማ ተሳክቶ ቤት እየመታ ሲገባም እንደ ሚከተለው ነው ።
የተሠመሩት የጎብር ቃላት ናቸው ።

ስለ ዐቢይ ጾም ፡

(ሀ) ከሞተብሽ ወዲህ ግድፍት ወንድምሽ ።
ቅቤ ባትቀቢ ንጹት ቢበላሽ
የኛ ጾም ወይዘሮ ሰው ሁሉ ጠላሽ ።

(ለ) በጣም አስቀየመች የእኛ ጾም ሳዱላ ።
ጥሉላት አልበላም አልቀባም ብላ ።

(ሐ) ባሕታዊ ጐበዝ ጠሙን ከዱር ውሎ
ማታ ሲሮጥ መጣ ዐይኑ ቅጠል መስሎ ።

(መ) ጸምን አጠቃለሁ እገላለሁ ሲል ።
ይኸው ነሆለለ መሰለ ቅጠል ።
(ሠ) አስማተኛ መናኝ ተምሮ ጥበብ ።
በቅጠል ገደለው ጠላቱን ረሃብ ።
(ረ) ራብ እንዳይቀጥል ስስት ሥራውን ።
በቅጠል ፈዘዘ ሆነ ምናምን ።
(ሰ) ሆድ ሀገር ሲያቃጥል ቂያ እሳት ራብ ።
በቅጠል አጠፋው ባሕታዊ ሕዝብ ።
(ቀ) የባሕታዊ ልጅ ሲፈልግ ልዕልና ።
የክርስቶስን ምሽት ትላንት ወሸመና ።
ቅጠል ብታበላው ሁኖ ቀረ መና ።
(በ) በጣም ያሳዝናል የልጅ ራብ ሞት ።
እወጣ እወጣ ሲል ሲጥር ዘለለት ።
ባላንጋራው መናኝ ትላንት መጥቶ ድንገት ።
አፈዘዘው አሉኝ በቅጠል መድኃኒት ።

ስለ ክረምት፡

(ተ) መቄማመጥ ኩታ ዕዩት ሲያምርብኝ ።
ከክረምት ዘመቻ በለስ የሰጠኝ፡
ትላለች ወይኒቱ ካፋፉ ላይ ሁና፡
ልብሷን ልትጥለው ነው አይደለችም ደኅና ።
ዕይዋት ተመልከቷት ራቁቷን ናት ።
ኩታዋን ወርውራ እኔው እንዳልሁት ።
(ኀ) ወይዘሮ ወይኒቱ ደኅናም አይደለች፡
በጋ ባኗ ሙቶ ደም ታለቅሳለች ።

ከሀገራችን እልቅሶና ዘፈን፡

(ነ) ምን ቅጠል ናት ብዬ አሻግሬ ሳይ፡
ያች ሐረግ ሬሳ መሆኗ ነው ወይ ።
(አ) ምን ያሉ ቄስ ናቸው የማይጠብቁ ዕቃ ።
ከቤተስኪያን ጓሮ ዕጣኒቱ ወድቃ ።
(ከ) መልካም እንኳ አይደል ቄንጅነቴ፡
ይጓጉበታል በቤቴ ።
(ወ) ምነው ጌታዬ ምነው፡
እኔን ሲል ያልቃል ሰው ።

በላይ የሚባል ሰው ወዳ ፡

(ወ) ወባይ ውኃ ሞልቶ ባያሻግርህ ፡
በላይ አትመጣም በተኃ ዙረህ ።
ክንፉ የሚባል ሰው የወደደች ሴት የገጠመቸው ግጥም
(ዘ) ዶሮም ያረዳችሁ ቆቅም የያዛችሁ
እቤቴ ላኩልኝ ክንፉን እባካችሁ
(የ) ተምሮ ተምሮ ለቅዳሴ ደርሶ
ልጇ ከማጠኔ ገባ ተመልሶ ።
ልጅዋን ከተማሪ ቤት እሳት የበላባት
(ደ) ይማርልኝ ብዬ ዋሽራ ሰድጇ
ቀለም ገባው አሉ እሳት ሆነ ልጇ ።
ውኃ የበላባት ፡
(ገ) የልጇን ደመኛ ከቤት አገኘሁት
ልቤ ቢደነግጥ ውኃ ቢሆን ተውሁት ።
ሁለቱን ልጆቿን አንድ የሚባል ወንዝ የወሰደባት
መርጠሽ የምትባል ሴት እኅትና እናቲቱ ያለቀሱት
(ጠ) ሁለቱን አንድ ዘንድ ለምን ሰደድሻቸው
መርጠሽ ከልጆችሽ ባስቀረሽላቸው ።
መልስ ፡
ካንድ ሁለት ይሻላል ብዬ ብሰዳቸው
ኮርክ ላይ መጣልኝ የሁለቱም መርዷቸው ።
(ጰ) የሰፈዱን እኽል ዶሮ በላብሽ
እሽ ! በይ አንች ልጅ ሰው ፈረደብሽ
(ጸ) የሰፈዱን እኽል ዶሮ እየበላባት
እሽ ! ስትል ጊዜ እንዴት አማረባት ።
(ፀ) ምነው ባደረገኝ የደጅዋን ትንኝ
ከከንፈሯ ሁኜ እሺ ! እንድትለኝ ።
የተማሪ እናት በሌለበት ሙታ ለልቅሶ ወደ መቃብሯ ቢሄድ ሙችካይ ሰውነቷ
ን ሁሉ በልቶ አንጀቷን ብቻ ጥሎለት ሂዶ ስላገኘ የሚከተለውን አለቀሰ ።
(ፈ) እንኳን አልሞተብኝ አብሮ አልተቀበረ
ቀድሞም የሚያዝንልኝ አንጀቷ ነበረ ።
የምሥራች የምትባል ሰው ሙታ እናቲቱ ያሰለቀሰችው ፡
(ፐ) እንደ ወዲያ ሰዎች እንደ ወሰንተኛ

የምሥራች ሞተች የሚሉ አማርኛ ።
እኛም ብንናገር ሰውም ብንጠይቅ
የምሥራች ሞተች ተብሎም አያውቅ ።
ስለ ጎብር እስከ ዚህ ይብቃና ምርምር ወደሚባለው ደግሞ እንሻገር እስኪ ።

፫ ምርምር ፡

ጎብር የጋራ ሲሆን ነው ብለናል ፡ ይኸውም የስም ክፍል እንጂ የግሥ ክፍል አይደለም ። የግሥ ክፍል በጎብርነት የመጣ እንደሆነ ጸደቀ እንደሚባልና ከጸያፍ እንደሚቈጠር አስረድተናል ፡ ምርምር ግን ቃሉን ወዲያና ወዲህ አማትቶ ግዕዙን ወደ አማርኛ አማርኛውን ወደ ግዕዝ አዘውሮ እያንዳንዱ ቃል ከፋፍሎና መላልሶ ሲያዩት የሚገኘው ፍች ነው ። አብዘኛውን የሴት ወይዘሮና የወንድ መኳንንቱ እልቅሶ ፡ ዘፈን በገና ቀረርቶ የሚነገረው በጎብርና በምርምር ነው ።

በስድ ሲነገር እንደሚከተለው ነው። አለቃ ተክሌ ዘዋሽራ አንድ ቀን በሸማኔዎች ደጅ ሲያልፉ በዓል ኑሮ ከመንገድ ዳር ከደምበር ላይ ተቀምጠው ወሬአቸውን ሲጠልዙ ስለ ደረሱባቸው ደንግጠው ይኑሩ ለማለት ሲነሡ አንዱ ሲሳተው ሰሙና ዛሬስ ምን ሁና ችኋል አትቋጥሩም እንዴ ! ከዚህ ፈሳችሁ በሥራ ምድር ፡ በጻድቃን ተቀመጡ ብለው ካለፉ በኋላ ያው የተሳተው ሰው ተከትሎ ዐወቁኝ አላወቁኝም እያለ እሳቸውን ጠይቆ ለመረዳት ይህን ያደረገው ማን ነው መምህር ቢላቸው ፡ እኔን የምትጠይቀኝ አንተ አልነበርህም ወይ ብለው መለሱለት ።

ምርምሮች ፡ አትቋጥሩም ወይ ፡ ከዚህ ፈሳችሁ ፡ አንተ አልነበርህም ወይ ናቸው ።

በቀን ዐይታ ጆሮ አማራት ፡ በ ቀን ዐይታ እንደ ቀ ጆሮ አማራት ማለት ነው ፡ ዥጉ ሲሄድ ምን ይመስላል ዥጉ ሲሄድ የምን ሆሄ ይመስላል ።

አንተ ቅን ነህ እንደ ቅ ጠማማ ነህ ። ዘን ጣፍ (ዘንጣፍ) ። ጽሕፈትህ ስላማረ ምን ጣፍ ምንጻፍ ። አንድ ሴትዮ ከተማሪ ጋራ መወሰለቷ ተሰምቶ በሷ ጓደኞቹን ይዘ ሊገለው ቢመጣ እንዳትነግረው ከሰው መካከል ስለ ሆነበት ፡ ሽምብራ ሼት ገዝታ ለሁሉም ካደለች በኋላ እንካ ተሜ አንተም ጠርጥር ብላ ጣለችለት እሱም ይህን እንደሰማ ሾልኮ በረረ ። በምርምር ጊዜ የሚጸፈው ሰሙ ነው እንጂ ወርቁ አይደለም ። በዜማም ተሳክቶ ሲነገር እንደሚከተው ነው ።

(ሀ) አንዱ ይበቃል የወንጌል ቃል
አለመስጠት ያጸድቃል
መስጠት ያጸድቃል አለ ማለት ነው ።

(ለ) ገዝቼ ነበር ጥገት
እጠጣ ብዬ ወተት
ቅሌ ተሰብሮ አገናለሁ
በምን አልባታለሁ (በምንአልባት አለሁ) ።

(ሐ) የሰጠኸውን እየሰጠ ይባልብሃል አንቱ
አታበላሸው ገንዘብህን
ወይ አንተ ተመስገን ።

(መ) ከዚያ ቤት ያሉ ዋንጮች
ታናናሽ ናቸው ነጫጮች
በእኒህ ጠጥቼ ምን ሊጠቅመኝ
በተሰቀለው ስጠኝ

(ሠ) ማሰለፍማ ታውቃለህ
አትሰጥም እንጂ ከጠላህ ።

(ረ) ትንሽ ውኃ አሙቄ ሳላስመልሰው
አረ ገና አሞቱ ከራሴ ላይ ነው ።

(ሰ) ጐንደር ወርጄ ተክኜ
ልብሰ ተክኖ ለብሼ
ታዩኛላችሁ እኔን ፡
ነገ ገብቼ ሳጥን

እማሆይ ወለተ እግዚአብሔር የምሳና ቅርፍት ትንበኽ አስመስለው ሽጠው ራታቸውን ገዝተው ስለበሉ በበነጋው የሚከተለውን ቅኔ ተናግረዋል ።

(ቀ) ጊዜ እንዲህ ይገፋል እየወሰለቱ
ምሳና ራት ሆነኝ ትላንት የሸተጥሁቱ ።
ወዬ ቴዎድሮስ ለእቴጌ ምንትዋብ ያለቀሱት ፡

(በ) እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሄድ
እቴጌ ምንትዋብ ሚስትን ናት ገረድ ።

(ተ) እጅግ ሥር ወዋቂ ትላንትና ሞተች
መድኃኒቱን ምሳ ታበላኝ ነበረች።
ራስ አሊ ፡

(ኀ) የጣቴን ቀለበት ሰጠሁት ለካሣ ።
በኔማ ጣት ገብቶ አስጨነቀኝሳ ።
ደራሲው ፡

(ነ) ካንቺ ጋር ሚጫወት በጣም የደላው
አቶ ሥራ የለሽ ባለ ጊዜ ነው ።

(አ) ብዙ ነገር ሳስብ ወርቅነሽ ቢሉኝ
መቼ ብረት ሁነሽ አፈር በላብኝ ።

(ከ) እሾኹን ጉልጥምቱን ሚያናቅፈውን
ጠቅል ጠርጎልሃል አንት አስፋ ወሰን

(ወ) አፍሪካ በመላ ተዝርግቶ ሳል
ሁሉንም ሰብስበው ተነሣ ጠቅል ።

ኅብርና ምርምር ቅኔያቸው ጣፋጭና ቀላል ስለሆነ እስከ ዚህ በቅቶን ወደ አንጻር እንሻገር ።

፬ አንጻር ።

አንጻረ አቀና ፊቱን መለሰ ፡ አመለከተ ከሚለው የመጣ ስለሆነ ፡ አንጻር ትይዩ ማለት ነው ። በዘመናችን ቅኔ ቤት ያልደረሱና ፡ ቅኔ ምን እንደሆነ ያላወቁ መምህራንና ይልቁንም ደራስያን ነን ብለው ስለሚያስቡ ፡ ቅኔ ግጥም ሁኖ በጠቅላላው እንደ ጠፋና ከዚያውም ያንጻር ትርጉም እንዲህ እንበለው በመባል ልዩ ልዩ እንግዳ ደራሽ ውኃ ፈሳሽ ትችት እየተሰጠው መበላሸቱን እናውቃለን ፤ ቢሆንም ደምበኛውን ፍች ከዚህ በታች ሰጥተናልና ወዋጁን በደምብ አጥንቶ ፡ ሕጋጌውን ተረድቶ አንበቢው ወደ እውነተኛው መንገድ ይመለስበታል የሚል ተስፋ አለን ። በዚህ ክፍል የሚገኘው ቅኔ ግብረ አበርነት ሊኖረው ያስፈልጋል እንጂ እንደ ስድ ንባብ በእንደ መነጻጸር የለበትም ። ም. ቴዎድሮስ እንደ ናፖሌዎን አሸናፊ ነበረ ቢል የስድ እንጂ የቅኔ ተነጻጻሪ ለመሆን አይችልም ፤ የቅኔው ግን እንደሚከተው ነው ፤ ሀ) ግብፐ ድል አሰናድቶ ቴዎድሮስ ናፖልዮንን ጠራው ። ቴዎድሮስና ናፖሌዎን በለካባ ከባለካባ ነውና እንጠራራ ተበባሉ። ሐ) ሰሎሞን ኃይለ ሥላሴን የሠራሁትን ጥበብ ዕይልኝ ብሎ ጋበዘው ። ሁሉም በሰምና ወርቅ ደምብ የተመሰለ እንደሆነ ድርብ ፡ ራሱ ብቻ የሆነ እንደሆነ ግን ነጠላ አንጻር ይባላል ።

ም. መምህር ገበሬ ትምህርት እህልን ሲዘራ ምሽቱ ተማሪ ዕውቀት አትክልትን ስትኰተኵት አሸክራቸው ትጋት ስንፍና አረምን ያርማል ። በግዋምና በቤትም ሲሰናዳ እንደ ሚከተለው ነው ።

ነጠላ አንጻር ከደራሲው ስለ ጸደይ ።

ጸደይ ልትመጣ ነው ደገሰች አበባ ፡
ቍንን ተሰናድታ አቀረበች ከልባ
አደይም ጀመረች ቀይ ቀለም ትቀባ
በለስ ከተፍ አለች ሰውነቷን ታጥባ
ከወይኒቱ ጋራ አደራሽ ልትገባ ፤
መሬት አነጠፈች ለምለም እሣርን
ምድር ጐዘጐዘች ቅጠል ምንጣፍን ፡
በጣም ደስ እንዲላት መኖሪያቸው ደን
በመቱ የምትመጣ ወይዘሮ ጥቢን ፤
ጅረት ስታቀብል የጠጁን በተኃ

ምንጭ ይዛ ደረሰች እጅግ የጠራ ውኃ
መታጠቢያ ሚሆን ደግሞውንም ሚጠጣ
ወይዘሮ ልምላሜ በጽጌ ስትመጣ ፤
ይህን መሰናዶ ዐይታ ጽጌረዳ
በጣሙን ገረማት መሰላት እንግዳ ፡
ዓጋም ድንገት ደርሶ ሁሉም ሲሰናዳ
ዙሮ እየነገረ ለዘመድ ለባዳ
ከአብታ ጋር ሁኖ በሳቅ ሊፈነዳ ።

ድርብ አንጻር ከደራሲው ስለ ክረምት ፤

ጀግናው በጋ ሙቶ የወይኒቱ ባል ፤
ራምኖን አለች አረ እሰይ እልል !
ጠላቷ ነውና ጥንቱንም ሲቈጣ
ራቅቷን አርጎ የሚያሳያት ጣጣ ።
አብራ ታለቅሳለች ወይዘሪት በለስ
እሱ ነበርና የሚያለብሳት ልብስ ።
ቀረ ወዬው አለች ቀሚሴ ልምላሜ
ያለልብስ ከመኖር በቀረብኝ ዕድሜ ።
የጎረቤት ልቅሶ ለሌላው ሠርጉ ነው
ከቴ ራምኖን ቤት ይሰማል ቻቻታው
ወይኒቱና በለስ ፊታቸውን አቅልተው ፡
ሐዲ ሊገሥጹ ወደ ጠላታቸው
ዘፈን ልምላሜዋን እንድትተው ለጊዜው ።
እነዚህ ተጣልተው አንቺ ክቺ ሲሉ
የመንደር ወይዘሮች ደመናት በሙሉ ፡
ሲሰሟቸው ጊዜ ፡ በመብረቅ ጥርሳቸው
ይስቁ ጀመረ ወዲያው ከፊታቸው ።
መርገፍ ግፍን ዐይታ ባልቴት ሰማይም
ታረግፈው ጀመረ እንባዋን ዝናም ።
ይህንን ጭቅጭቅ ሰምቶ ከመንገድ
በጣሙን ተቈጣ ሽሜ ነጐድጓድ ።

ከዚህ በላይ ያሉት ቅኔዎች የጸደይንና የክረምትን ጣጣ ለመግለጥ የቻሉት በአንጻርነታቸው እንደሆነ ያስተውሏል ። የመጀመሪያው የሰምና ወርቅ ጣጣ ስለሌለበት ነጠላ ዳግመኛው ግን በሰምና ወርቅ ደምብ ስለተሠራ ድርብ አንጻር ይባላል ። አንጻር በጣም አስደሳች ስለሆነ ብዙ ቅኔ ተደርሶበታል ። ደኅና አድርጎ ለመረዳት የላሊበላን ቅኔ በደንብ ያነቧል ፤ እሱም አብዛኛው ነጠላ አንጻር ነው ።